የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No.10
ADDIS ABABA 2nd November, 2004

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፭/፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ለመንግሥት ዘርፍ አቅም ግንባታ ፕሮግራም ድጋፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ....ገጽ... ፪ሺ፱፻፴፱

**CONTENTS**

**Proclamation No. 425/2004**

International Development Association Credit Agreement for Financing the Public Sector Capacity Building Program Support Project and Sanitation Project Ratification Proclamation No. Page 2939

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፭/፲፱፻፺፯

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለመንግሥት ዘርፍ አቅም ግንባታ ፕሮግራም ድጋፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፷፮ሚሊዮን፱፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (ስድሳ ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ኦገስት ፳፫ ፪ሺ፬ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኤኮኖሚ ዓለም ዐቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መፅደቅ ስላለባቸው፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 425/2004.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** a Credit Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of sixty six million nine hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 66,900,000) for financing Public Sector Capacity Building Program Support Project was signed in Addis Ababa on August 23, 2004;

**WHEREAS,** basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its session held on the 2nd day of November, 2004;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Article (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለመንግሥት ዘርፍ አቅም ግንባታ ፕሮግራም ድጋፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፭/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. አገስት ፳፫ ቀን ፪ሺ፬ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመው ቁጥር 3899 ET የብድር ስምምነት ነው።

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፷፮ሚሊዮን፱፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (ስድሳ ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Credit Agreement for Financing the Public Sector Capacity Building Program Support Project and Sanitation Project Ratification Proclamation No. 425/2004."

## 2. Definition

In this Proclamation "Credit Agreement" means the Credit Agreement No 3899 ET signed between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association on August 23, 2004.

## 3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of sixty six million nine hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 66,900,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the 2nd day of November, 2004.

**Done at Addis Ababa, this 2nd day of November, 2004.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት